የካቲት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

# ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል እና ሚስተር ሚካኤል ጎንዛለስ አብረው ለመስራት ተስማሙ

## የፕሬዝደንት ባራክ ኦባማ አዲሱ አስተዳደር ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት እንደገና የሚመረምር መሆኑ ተገለፀ::

ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ሊቀመንበር በኢትዮጵያ የአሜሪካ ኤምባሲ የፖለቲካ-ኢኮኖሚ አማካሪ የሆኑትን ሚስተር ሚካኤል ጎንዛላስን የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም በጽህፈት ቤታቸው ተቀብለው አነጋገሩ:: የአሜሪካን ባለስልጣኑ ኢንጂነር ኃይሉ ጋር ቀጠሮ የጠየቁበትን ምክንያት ሲያስረዱ መንግስታቸው መኢአድ የኢትዮጵያን ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ እንዴት እንደሚመለከት ለማወቅ ይፈልጋል ብለዋል::

ኢንጅነር ኃይሉ የወቅቱን የኢትዮጵያን ሁኔታ ሲያስረዱ ከ1997ቱ ብሔራዊ ምርጫ ወዲህ የፖለቲካ ሁኔታ እየተባባሰ መጥቶ አሁን መጥፎ ደረጃ ላይ መድረሱን ገልጸዋል:: የፓርቲያቸውና የሌሎችም ተቃዋሚ አባላት በገዢው ፓርቲና መንግስት አባላት እንዲዋከቡ እየተደረጉ ከመሆኑም በላይ እንግልቱና እሥራቱ እየቀጠለ ነው:: በሚዲያውና በፍትህ አካላቱ ላይ ያለውም ተፅዕኖ አላቋረጠም::

ቀጥለውም ሲያብራሩ በብሔራዊ ምርጫ ማግስት የገዢው ፓርቲና መንግስት በምርጫው ላይ የደረሰባቸውን ሽንፈት ለማካካስ ባደረጉት ጥረት ፓርቲያቸው ቅንጅት ለአንድትና ለዲሞክራሲ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር በመተባበር የጠየቀው ሰባት ሀሳቦች በገዢው ፓርቲ ተቀባይነት እስካላገኙ ድረስ ሁኔታው በጣም አስጊ መሆኑን ይቀጥላል ብለዋል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት የታገለላቸውና የተሰዋላቸው ነፃነት፣ ፍትህና መልካም አስተዳደር ሰፍነው ህይወቱ ተለውጦ የተደላደለ ኑሮ መኖር እንዲችል፣ ገዢው ፓርቲና መንግስት በኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት እንዲፀድቁ የተደረጉት ሕጎችና ደንቦች ከአዲስ አበባ ጀምሮ በእየከፍለ ሀገሩ እስከ ቀበሌ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች ሁሉ ባለስልጣኖች እንዲያከበሩት እንዲያደርግ ጠይቀዋል::

መኢአድና ገዢው ፓርቲና መንግስት እንዲያከብራቸው ያነሳቸው እነዚህ ሰባቱ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት የሚደገፉ ሲሆኑ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ብለዋል ኢንጅነር ኃይሉ::

1ኛ/ የፓለቲካ እስረኞች ካለንዳች ቅደመ ሁኔታ እንዲፈቱ፣

2ኛ/ የመገናኛ ብዙሀንና የፕሬስ ነፃነት እንዲከበር፣

3ኛ/ ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ የምርጫ ባርድ እንዲደራጅና የምርጫ ሕጉ የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በሚያዘውና በሚፈቅደው ነፃነት መሰረት እንዲስተካከል፣

4ኛ/ የፍትህ አካላት ማለትም አቃቤ ሕግና ዳኞች ካለ ገዢው ፓርቲ እና መንግስት ጣልቃ ገብነትና ተጽዕኖ የህግ ማስከበርና የዳኝነት ሥራቸውን በነፃነት እንዲያከናውኑ እንዲደረግ፣

5ኛ/ የመከላከያ እና የፖሊስ ኃይሎቻችን የኢትዮጵያ ሕገ መንግስት በሚያዘው መሠረት ከወራሪ ኃይል የኢትዮጵያን ሕዝብ እና ዳር ደንበር፣ እንዲሁም ህዝባችንን ሕግን ተከተትለው ከእርስ በእርሱ እንዲጠብቁ፣ ገዢው ፓርቲና መንግሥት እንዲያደርግና ሕዝብን ለማስፈራራትና ለመጉዳት መጠቀሚያ ማድረጉ እንዲቆም፣

6ኛ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በፈለገው የፓለቲካ፣ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ድርጅቶች በነፃነት የመደራጀት እና የመንቀሳቀስ መብቱ እንዲከበርለት፣ እና

7ኛ/ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ፣ ድርጅት እና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሠላማዊ መንገድ ሀሳባቸውንና ተቃውሚቸውን ለመንግስት በመረጡት ስልት በነፃነት የመግለፅ ፍፁማዊ መብታቸው ሳይገረሰስ እና ሳይሸረሸር እንዲከበርላቸው የሚሉ ናቸው ብለዋል ኢንጅነር ኃይሉ።

በመኢአድ እምነት እነዚህ መብቶች በገዢው ፓርቲ እና መንግስት መታፈናቸው እስከ ቀጠለ ድረስ የኢትዮጵያ የፖሊቲካ ሁኔታ ተለውጦ ህዝብ በሠላማዊ መንገድ የመረጠውን መንግስት የማግኙቱ ጉዳይ ስጋት እንዳደረባቸው ኢንጅነር ኃይሉ አበክረው ገልጠዋል። ቀጥለውም ኢንጂነር ኃይሉ ሲናገሩ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነት ህዝባቸውን ማንቀሳቀስ እስካልቻሉና ገዢው ፓርቲና መንግሥት በሠላማዊ መንገድ የኢትዮጵያን ሕዝብ ምርጫ የማያከበር ከሆነ መጪው ጊዜያት ጨለማ ሊሆን እንደሚችል ገልጸዋል።

ሚስተር ጉንዛለስ በመኢአድ የኢትዮጵያ ፖሊቲካ ግምገማ ሙሉ በሙሉ የሚስማሙ መሆኑን ገልፀው፣ ለዚህም ገዢው ፓርቲ እና መንግሰት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደህንነት፣ ልማትና ብልፅግና ሲባል መኢአድን ጨምሮ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በመግባባትና በስምምነት መስራት እንደሚገባቸው በአፅንኦት ገልፀዋል። ጨምረውም ሲናገሩ፣ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ቀንድ ታላቅ ሀገር በመሆኗ አዲሱ የፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ የአሜሪካ አስተዳደር በኢትዮጵያ ላይ የሚከተለውን መመሪያ እንደገና ለመርመር ዝግጁ ነው ብለዋል ሚስተር ጎንዛላስ። ከዚህ አንፃር አሉ ሚሰተር ጎንዛለስ፣ የአሜሪካን መንግስት እስካሁን ሲከተል የነበረውን የወታደራዊ ኃይል ትኩረት ከኢትዮጵያ ህዝብ ልማትና ዕድገት

ጋር የሚያጣጥምበትን ፖሊሲ ይቀይሳል ብለዋል:: በተለይም፣ አሉ ሚሰተር ጉንዛላስ፣ በተለይም መላው የኢትዮጵያ ህዝብና ተቃዋሚ የፖሊቲካ ፓርቲዎች በነፃነት መንቀሳቀስ መቻል አለባቸው፣ በነፃነት ሀሳባቸውን በፈለጉት ዘዴ በሰላማዊ መንገድ መግለፅ አለባቸው፣ የፍትሕና የሕግ የበላይነት አካላት ከገዢው ፓርቲና መንግስት ነፃ ሆነው የኢትዮጵያን ህዝብ ማገልገል መቻል አለባቸው ብለዋል:: ባጠቃላይ መልካም አስተዳደር በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ገዢው ፓርቲ እና መንስግት ያላሰለሰ የፓለቲካ ፈቃደኝነት ማድረግ አለባቸው ብለዋል::

በመጨረሻም ሚስተር ጎንዛለስ ሲናገሩ የገዢው ፓርቲና መንግስት ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በሠላም እና በመከባበር አብረው በመስራት የመጪውን የሁለት ሺህ ሁለት ዓ.ም የኢትዮጵያን ብሔራዊ ምርጫ እንዲሳካ በማድረግ፣ ሥልጣን በሠላማዊ መንገድ የመሸጋገር ዕድል እንዲያገኝ ማስቻል አለባቸው ብለዋል:: በተጨማሪም አሉ ሚስተር ጎንዛለስ የኢትዮጳያ ህዝብ እና ተቃዋሚ የፓሊቲካ ፓርቲዎች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱ ከላይ በተቃዋሚ የቀረቡት ሰባት ጥያቄዎች በኢትዮጳያ ሕገ መንግሰት ውስጥ የተነደገጉ በመሆናቸው ገዢው ፓርቲና መንግሰት ሕጉቹ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ሁኔታዎችን እንደሚያመቻቹ ተስፋ እንዳላቸው ገልፀዋል:: ይህ ባይሆን፤ ግን አሉ ሚሰተር ጎንዛላዝ እርሳቸው እንደ ኢንጅነር ኃይሉ ሁሉ በኢትዮጵያ አደገኛ ጊዜ እንደሚታያቸው ስጋት እንዳለቸው ገልፀዋል::

በኢንጀነር ኃይሉ ሻውልና በሚሰተር ጎንዛላስ መካከል የተደረገው ውይይት በፍፁም መግባባትና መከባበር የተካሄደ ነበር:: ሚሰተር ጎንዛለስ በስብሰባው ማጠቃለያ ሲናገሩ የአሜሪካን ኤምባሲ ከሌሎች መንግስሥታት፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች እና መኢአድን ጨምሮ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር በህብረት በመስራት የመናገር፣ የመፃፍ፣ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ እና በሰላማዊ መንገድ ሰዎች፣ ድርጅቶችና መላው የኢትዮጵያ ህዝብ በነፃነት ሀሳባቸውን የመግለጽ መብቶቻቸው እንዲከበሩ፣ የፍትሕ አካላትና የሕግ የበላይነት እንዲሁም የሚዲያ አካላትና አባላት ከገዢው ፓርቲና መንግሥት ተፅዕኖ እንዲላቀቁ እንዲሁም መልካም አስተዳደር በኢትዮጳያ ሰፍኖ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ የፖለቲካ ኢኮኖሚ የመገንባት ችሎታው እንዲዳብር ያላሰለሰ ጥረት እንደሚያደርጉ ቃል ገብተዋል:: በተጨማሪም አሉ ሚሰተር ጎንዛለስ፣ መኢአድን ጨምሮ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመጪው 2002 ብሔራዊ ምርጫ በነፃነት መንቀሳቀስ እንዲችሉ የአሜሪካን መንግሥት ከሌሎች መንግሥታትና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር በሕብረት እንደሚሰራ አረጋግጣለሁ ብለዋል::